ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 8 ቁጥር 1 የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም.

# የካቲት 1966 እና ያ ትውልድ

*(የካቲት 1966 ዓ.ም. 47ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=lDHtlI1SQhA )*

የካቲት 1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ከፍተኛው ቦታ የሚሰጠው ነው። ከሦስት ሺህ ዘመን ተያይዞ የመጣውን ንጉሳዊ አገዛዝ የነቀነቀ፣ ባላባታዊ ፊውዳላዊ ሥርዓትን ያናጋ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በመሆኑ በታሪክ ተጠቃሽነት ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። የባላባታዊ የመሬት ሥሪት ያስመረረው አፈር ገፊ ጭሰኛ የተጠራቀመ ብሶት፣ የከተሜው ላብ አደር ቅጥ ያጣ ብዝበዛ፣ በፆታ ልዩነት ምክንያት በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደርሰው በደል፣ በሃይማኖት በኩል ያለው አድልዎ የፈጠረው ስሜት፣ የወታደሩና የሠራተኛው ክፍል ዝቅተኛ የኑሮ ሕይወት፣ የተማሪዎች የየዕለት ለውጥ ፍላጎትና ለተበዳዩ ሕዝባቸው የሚያሰሙት ጩኸት የዱላና ጥይት ምላሽ ጥርቅም ውጤት የካቲት 1966ን ሕዝባዊ አመጽ ወለደ። የበደል፣ የጭቆና፣ የኋላ ቀርነት፣ የረሃብ፣ የመብት ረገጣ ውጤት አመጽ ጸንሶ፤ አመጽን አርግዞ፤ ሕዝባዊ ንቅናቄን በመላ ኢትዮጵያ ተገላገለ። ልክ የዛሬ 47 ዓመት የካቲት 1966 ዓ.ም.።

የካቲት 66 ሲነሳ ይበልጡን ለእንቅስቃሴው ከፍተኛ መጋጋልና የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ እርሾ የሆነው ከኅሊናና ከአዕምሮ የማይፋቀው የወሎ ረሃብ መጋለጥ ነበር ቢባል ሃቅነቱ የማይካድ ነው። ወሎ ተርቦ በየደቂቃው ሕዝብ ሲያልቅ፣ ማንቁርታቸው ያገጠጠ፣ ዓይናቸው የሰረጎደ፣ ቆዳቸው ከአጥንታቸው የተጣበቀ ሕፃናት ተንዘልዝሎ የደረቀ የሟች እናቶቻቸውን ጡት ሲምጉ ማየት ሰውነትን የሚቆነጥጥ፣ ዕንባንና ሲቃን የሚያከናንብ ሰቆቃ የንጉሡን ታማኝ ኃይሎች ሳይቀር ያስቆጣና ያሳመጸ ጉዳይ ነበር።

በተለይ ከ1953 ዓ.ም. የግርማሜና መንግስቱ ነዋይ በንጉሡ ላይ የተደረገ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ የተማረው ክፍል የነበረው ባላባታዊ ሥርዓት ላይ የሚያካሂደው እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መምጣትና ጥያቄዎቹም ከአካባቢያዊነት አልፈው ፖለቲካዊ ይዘት እየያዙ መምጣት ጀመሩ። ቁጥሩ ቢያንስም በወቅቱ አንድ ጥላሁን በሺህ ታጋይ ይታሰብ ነበርና ጥላሁን ግዛው ላይ በንጉሡ ወታደሮች የተወሰደው እርምጃ ይበልጥ ተማሪውን አነሳሳ። ከሕዝብ በሚሰበሰብ ቀረጥ የሚማረው ተማሪ ወገንተኛነቱን ለተበዳዩ ሕዝብ ሰጠ። ትልቁን የባላባታዊ ሥርዓት ማናጊያ መፈክሩን ይዞ ግምባር ቀደም ፋና ወጊ ሆነ "መሬት ለአራሹ!"።

ላብ አደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ምሁሩ፣ ወታደሩ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ወዘተ የትግሉ አጋር ይሆን ዘንድ ተሜ ሀገሬ ኢትዮጵያ እያለ መቀስቀሱን ጀመረ።

«አትነሳም ወይ፤ አትነሳም ወይ፡ የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ፡ ተነስ! ተነስ!

«አትነሽም ወይ፤ አትነሽም ወይ፡ የግፍ አገዛዝ አይበቃሽም ወይ፡ ተነሽ! ተነሽ!»

በዝማሬው፤ ጭንቅላቱ የፖሊስ ዱላን አስተናግዷል። በቦተርና ሌሎች ማጎሪያ ስፍራዎች እንዲማቅቅ ተደርጓል። የጥላሁን፣ የዋለልኝና ማርታ ሞት ዝማሬውን አደመቀው፣ ትግሉን አጋጋለው።

«ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?
ዋለልኝ ለምን፤ ለምን ሞተ?
ማርታ ለምን፤ ለምን ሞተች?
በሃይል በትግል ነው
ነፃነት የሚገኘው።»

ዝማሬ ለትግሉ መስዋዕትነትን እንደሚከፍልበት አስተማረ። የዐድዋና የአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣልያን ወረራ ድል የመቶ ሺዎች ደምና አጥንት ውጤት መሆኑን ተገነዘበ

«ፋኖ ተሰማራ፤ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆችሚኒ፤ እንደ ቼኩቬራ
በዱር በገደሉ፤ ትግሉን እንድትመራ»

ዝማሬዎች የየሰልፉ ማድመቂያና መቀስቀሻ ሆኑ። ማንነቱን ለሕዝብ መብትና ነፃነት አሳልፎ ሊሰጥ የተዘጋጀ ትውልድ ተወለደ። ቅድሚያ ጩኸቱ ለሀገርና ለሕዝብ ያደረገ ትውልድ፤ ያ ትውልድ!

«ተው ስማኝ ሀገሬ፤ ኧረ ስማኝ ሀገሬ
ተው ስማኝ ሀገሬ፤ ሲከፋኝ ነው መኖሬ»

እንጉርጉሮ ትግሉን አጋጋለው። የካቲት 66 የተጠራቀመ ብሶት አምጦ፡ አምጦ የወለደው ሕዝባዊ አብዮት።

«ያ ትውልድ ተቋም» የየካቲት 1966 ዓ.ም. መታሰቢያ ስናስታውስ ለኢትዮጵያ ሀገራቸውና ህዝባቸው መብትና ነፃነት አኩሪ ታሪክ በደማቸው ጽፈው ያለፉ ወገኖቻችንን በማስታወስ ነው።

የተማረው ያ ትውልድ ***«ድሃ ድሃ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት»*** ብሎ ትምህርት ለሁሉም ብሎ የጮኸ ትውልድ ነው። ማንም የማንን መብት ሰጪና ነፋጊ አይደለም ብሎ ***«የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም»*** በአጥንቱ ከፍ አድርጎ ደሙን አፍስሶበታል። ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ***«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አሁኑኑ»*** መፈክሩ በሥልጣን ጥመኞች ባንዳዎችና ፋሽስቶች ጥይት ሕይወቱን ገብሮበታል። ***«የሴቶች መብት ይረጋገጥ»*** መፈክሩ ጀግና ሴቶችን ወደ ትግሉ አደባባይ አሰልፏል። ሕይወታቸውን እስከ ጽንሳቸው የከፈሉ ታሪክ የመዘገባቸው የትግል እመቤቶች አፍርቶበታል። ***«የሃይማኖት እኩልነት መረጋገጥ»*** መፈክሩ እስላምና ክርስቲያኑን በአንድ ዓላማ አሰልፎ፡ አስተቃቅፎ፡ አታግሏል። ***«የብሔር/ብሔረሰቦች መብት ያለገደብ»*** ጩኸቱ ኦሮሞው፣ ትግሬው፣ አማራው፣ ጉራጌው፣ ወላይታው፣ ሐደሬው፣ ሁሉም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ለምዪ ኢትዮጵያ በጋራ እንዲሰለፍ አድርጎታል። ***«የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ»*** መፈክሩ፤ እስርና ስቃይ አከናንቦታል። ይህ ነው እንግዲህ በየካቲት 66 ብቅ ያለው ያ ትውልድ መፈክር! ይህ ነበር ጩኸቱ !!!

የየካቲት 66 ዓ.ም. አብዮት መሪ በማጣቱ የታጠቀው ሠራዊት ክፍል የፖሊስና ጦር ኃይሎች አስተባባሪ ደርግ ብሎ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. በማወጅ ቅድመ ዝግጅቱን ካስተካከለ በኋላ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. በሞግዚት አስተዳደር ስም በትረ መንግስቱን ጨብጦ በሕዝብ ስም እየማለና እየተገዘተ የሕዝብን መፈክር ከፍ ያደረገውን ያ ትውልድ በመመተር 17 ዓመት በአዋጅና በዘመቻ አቅራርቶ፣ ጥይትና ቦንብ አርከፍክፎ፣ ሀገሪቷን በደም የወየበ ምድር አርጎ ያለፈ አገዛዝ ደርግ ኢሠፓ ነበር።

የካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በፋሽስት ደርግና አጃቢዎቹ ባንዳዎች አቅጣጫውን በመሳቱና፣ ጠረኛ አገዛዝ በመስፈኑ ሀገሪቱ ላይ ጥሎ ለሄደው ጠባሳ ተጠያቂ ለሀገሩና ለህዝብ የጮኸውን ያ ትውልድ ለማድረግ ዛሬም ለማደናገሪያና ላፈሰሱት የንጹሀን ደም ይቅር በሉን ከማለት ይልቅ ትክክል እንደነበሩ ሁሉ "ትግላችን፣ አብዮታችንና ትዝታችን" እያሉ ጆሮ ሲያደነቁሩ ይደመጣሉ። ለነሱ "ትግላችን" ከማለት ግድያችን፤ "አብዮታችን" ከማለት አገዳደላችን፤ "ትዝታችን" ከማለት መባነናችን ብለው መተረኩ የማንነታቸው ገላጭ ነውና ይመረጣል።

አንድን ቤተሰብ እንዳለ መግደል እውን ጀግነት ነውን? ከ12 -16 ዓመት ያሉ ታዳጊ ሕፃናትን አሰቃይቶ በመግደል፡ የየካቲትን ጎርፍ አቅጣጫውን በደም የቀየረው ፋሽስት ደርግ እንደነበር የ17 ዓመቱ አገዛዝ ምስክር ነው። እናትና ልጅን፣ አባትና ልጅን፣ ወንድምና እህትን አሰቃይቶ የገደለ መንግስት እያለ፤ የየካቲት 66 እንቅስቃሴ መሪ ማጣት የፈጠረው ፋሺዝም እውን በያ ትውልድ ሊላከክ ይገባዋልን? በወራት ልዩነት ወንድማማቾችን መግደል፣ በከልካሻ ወራዳ ተግባራቸው በሴቶች እህቶቻችንን አካል ተጫውተው መግደል ነበር የነሱ አብዮት፣ የነሱ ትግላቸው፣ የነሱ ትዝታ። አዎ! የካቲት 66 እንቅስቃሴ ስልጣን ላይ ያስቀመጠው ፋሺዝም ልጆችን በመግደል እናቶችን አሳብዱል፤ ወላጆችን የአልጋ ቁራኛ አድርጓል፣ አባትና እናትን በመግደል ሕፃናትን ወላጅ አልባ አድርጓል፤ እንደነ መላኩ ተፈራ ዓይነት ገዳይ ፋሽስቶችን ሽሽት በየዱሩና በየበረሃው የቀረውን ቤቱ ይቁጠረውና በሺዎች የሚቆጠር ሕፃናትና ወጣቶች ደም ዛሬም እንደ ጀግንነት ሲተረክ ያስተዛዝባል።

አዎ! የካቲት 66 ሕዝባዊ አመጽ በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ ሊመራውና አቅጣጫ ሊያሲዘው ያስፈልግ የነበረ የፖለቲካ ድርጅት ባለመኖሩ ጠብመንጃ የተሸከመው ወታደር ስልጣን ላይ ሊቆናጠጥ መቻሉ የእንቅስቃሴው አሉታዊ አካል ነበርና ሊዘነጋ አይገባውም። የደርግን አምባገነናዊና ፋሽስታዊ አካሄድ እየተገነዘቡ ከሕዝቡ ጋር ሆነው ትግሉን ማቀናበር ሲችሉ በድጋፍና ሂስ ስም ደርግን አሰልጥነው የደርግ እሳት እራት ከመሆን ያላመለጡ ኃይሎችም የማይዘነጉ የየካቲቱ እንቅስቃሴ ቅሪቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ሀገራችንን በልማት ጎዳና ተገቢውን ሥፍራ እንድትይዝና ሕዝቧም ከድህነትና ከድንቁርና ይላቀቅ ዘንድ ብርቱ ምኞት የነበረው ያ ትውልድ ታሪክ በተፈላጊው ደረጃ የተተረከ፣ የተፃፈና፣ የተሰባሰበ ባለመሆኑ ታሪኩን ለማጣመም ዛሬም በሰማዕታቱ ላይ ሊሳለቁ የሚሞክሩ መኖራቸው ሊደንቀን አይገባም።

ዛሬ የካቲት 1966ን ስናስታውስ ያ ትውልድን መቀስቀሳችን አይቀርምና ነው ያንኳኳነው። ያ ትውልድን ስናነሳ ለመብትና ለነፃነት የተከፈለውን መስዋዕትነት መዳሰስ ግድ ይለናል። መስዋዕትነቱን ስናነሳ አሳሪና ታሳሪ፣ ገዳይና ተገዳይ፣ አሳዳጅና ተሳዳጅ፣ አጥፊና አልሚ የታሪኩ ተጋሪ ይሆናሉና የየካቲትን ፍሬ በልቶ የሕዝብ ልጆችን ደም የጠጣው ፋሽስታዊ አገዛዝ ሀገሪቷ ላይ ለደረሰው ጥፋትና ምስቅልቅል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ዋናውን ኃላፊነት እንደሚወስድ በማስመር ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» የካቲት 66ን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ስናስታውስ ድሉን ለሕዝብ ለማድረግ፣ ሕጻናት በቁያቸው ተሸማቀው ሳይሆን ቦርቀው የሚያድጉባት ብሩህ ተስፋ ፈንጣቂ የሚሆኑበት፣ አዛውንት እናትና አባቶች በልጆቻቸው "የት ደረሱ" የሚሳቀቁበት ሳይሆን ለሀገር ልማት ለሕዝብ ዕድገት ደፋ ቀና የሚል አኩሪ ትውልድ የሚያዩበት፣ ኢትዮጵያ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ባህልና ቋንቋ የሚፈካባት ማራኪ ሀገር ለማድረግ፣ የሃይማኖት አድልዎ ሳይኖር ሁሉም እንደ እምነቱ ሀገሬ! የሚላት፣ የተፈጥሮ ሀብቷና የዱር አራዊቶቿ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያገኙባት፣ ታሪካዊ ቅርሶቿ በእንክብካቤ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉባት፣ ሉዓላዊነቷና አንድነቷ የተጠበቀች ሀገር ለማየት የተንቦገቦገው የአብዮት ማዕበል አቅጣጫውን እንዳይስት የተከፈለው መስዋዕትነት፣ በየቤቱ የጥይት እሳት የሆነው ያ ትውልድ ተጋድሎ ሕዝባዊ ድል አለማስመዝገቡ ቢቆጨንም፣ ቢሰማንም፣ ትግላቸውና መስዋዕትነታቸው ሁሌም በትውልድ እንደሚታወስ፣ እንደሚዘከር በርግጠኝነት በመናገር ነው። ከፍ አድርጋችሁ የወደቃችሁለት መፈክርና ዝማሬ ዛሬም ህያው ነው። የድሉ ተቋዳሽ ባትሆኑም/ባንሆንም ጩኸታችሁ ተጋድሏችሁ ለሀገርና ለሕዝብ እንደነበር ታሪክ ይመሰክርላችኋል። በከፈላችሁት መስዋዕትነትና በአደረጋችሁት ተጋድሎ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ዘላለማዊነት አረጋግጣችኋል።

**የካቲት 66ና የትግል ሐዋርያ ያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!**

**የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም. (February 17, 2021)**

**አባሪውን ግጥም ቀጣዩ ገጽ ላይ ያንቡ**

**ያ ትውልድ ተቋም**

**ድረ ገጽ ፡** www.yatewlid.org, www.yatewlid.com

**ኢሜል ፡** yatewlid@gmail.com

**ምሥለ ገጽ ፡** https://www.facebook.com/yatewlid.thegeneration

# ትግሌ ትዝታው






«ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታስሬ
መብቴን ላስከብር
ጨቋኝን ልሽር
ተነስቻለሁ ዛሬ
ይኸው ታጥቄሃለሁ ዛሬ»

እየተባለ የተዘመረው
ትግሌ ትዝታው ዛሬም ህያው ነው።

«ልቤ ቆርጦ ተነስቷል
የደም አክታ ያገሳል
ይኸው ቆርጫለሁ
አምጫለሁ»


ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ
Dr. Tesfaye Debessay
የኢሕአፓ አመራር አባል (EPRP Ledership Member)


ማርቆስ ሐጎስ
Markos Hagos

እየተባለ የተዘመረው
ትግሌ ትዝታው ዛሬም ህያው ነው።

«ማን ደባለቀው?
የምር ታጋዩን እኛ ስናውቀው
የምር ተኳሹን እኛ ስናውቀው
ታንክ ታቅፎ ጨረሱኝ ባዩን
ማን ደባለቀው?»

እየተባለ የተገጠመው
ትግሌ ትዝታው ዛሬም ህያው ነው።


ዳሮ ነጋሽ
Daro Negash

«አንቺ ጭቁን ተነሽ ታገይ፤ ተነሽ ታገይ
ለነፃነት፤ ለድርቡ ዕኩይ ስቃይ
ተጨቋኟ እህትዬ፤ እህትዬ
በቃሽ ተነሽ፤ አያዋጣም ሁሌ ዬዬ»


ከ15ቀ30 ሶፍያ አየለ ገ/መስቀል
Sofia Avele G/Meskel

እየተባለ የተዘመረው
ትግሌ ትዝታው ዛሬም ህያው ነው።

